# የምሁራን ደናቁርት!

በዲሲ፣ ሲያትል፣ ሆነውም ኣትላንታ
ከንቱ ሲሸርቡ፣ ሲያበዙ ሓተታ
በቲቪ ጦር ሜዳ፣ በፓል-ቶክ ንዝነዛ
በሕልም ይቃዦሉ ኣጉል ማታ፣ ማታ...

ለካይሮ፣ ለሶማል ሰርክ ሲጠኑ ደጅ
በሂለሪ ደጃፍ ሰርክ ሲጠኑ ደጅ
ደፋ-ቀና ሲሉ በልዩ ውዝወዛ
በዓለም መንግሥታት ሰርክ ሲጠኑ ደጅ...

ታይቶ ኣይታወቅም ይኽ ዓይነት ውካታ
እጅ ኣዙር ለጠላት ሆነዋል መከታ
ቀና ቢመስልም ኣለበት ጠምዛዛ
ስልጣን ኣይገኝም በከንቱ ውትወታ

የጥብቅና ሊቁ፣ የነገረ-ፈጅ
የኢኮኖሚስቱ፣ የቦምብ፣ የፈንጅ
የሃገር መሪነት መች እንዲህ በዋዛ...
ብዙ መስዋእትነት ይጠይቃል እንጅ!

“ከኛ በላይ ማን ሊቅ?” እያሉ ሲመኩ
ሆት ዶግ ሲያላምጡ፣ ሃምበርገር ሲያኝኩ
ጊዜያቸው ኣለፈ በዋዛ፣ ፈዛዛ
ዘመኑም ካዳቸው እነ ሆድ-ኣምላኩ።

ኢትዮጵያ እንደሆነች ትላንት ብትነሳ
ዛሬ ሩቅ መጥቃለች በዕድገት ገስግሳ
ነገ ለሚገቡ ከሳጥን ቃሬዛ
ፍዝዝ ብለው ቀሩ የደመ-ነፍስ ሬሳ።

ገ/ኢ. ጐርፉ።